# እድገቱ ለማነው?

# ክፍል ሁለት

# አክሎግ ቢራራ (ዶር)

የዚህ ሃተታ መሰረታዊ ሃሳብ የኢትዮጵያ ተከታታይ የድርቅ ረሃብ የአየር ጠባይ መለዋወጥ ሳይሆን የመጥፎ አገዛዝና፤ የተበላሸ አስተዳደርና የተዛባ የገቢና የኃብት ስርጭት ውጤት ሆኗል የሚል ነው። ድርቅ የትም አገር የሚከሰት መሆኑ የታወቀ ነው። ቁም ነገሩ ይኼን የተፈጥሮ ችግር ለመቅረፍ መንግሥታት ያለባቸው ሃላፊነት ምን ይሆናል፤ እንዴት ለክፉ ቀን ይዘጋጃሉ? ያላቸውን የተወሰነ ባጀት ለሚፈለገው ነገር ያውላሉ ወይንስ ያባክናሉ? የሚለው ነው። የኢትዮጵያን ተከታታይ የረሃብ ችግር ለመወጣት የኢኮኖሚው አመራር (ፖሊሲ) ዝቅተኛ አምራቾችን አጎልማሽ መሆን አለበት። አጎልማሽነት ከህዝብ ተሳትፎ፤ ከመሬት ይዞታ ሳይሆን ከባለቤትነት፤ ከዘመናዊ ግብዓቶች አግባብነት፤ ከመሬት አጠቃቀም፤ ከአካባቢ እንክብካቤ፤ ከመንግሥት መሪዎችና ባለሥልጣናት ተቆርቋሪነትና ህዝብን አፍቃሪነት፤ ከግልፅነትና ከሃላፊነት ጋር ቀጥተኛ የሆነ ግንኙነት አለው። በዛሬይቱ ኢትዮጵያ የእድገት መርህ እነዚህ አስፈላጊ የአመራር መስፈርቶች ፍጹም አይታዩም። ሁሉም ባለሥልጣናት የሚሰሩት የራሳቸውን ቤተሰቦች ጥቅም ለማሟላት ሆኗል። የእድገቱ ውጤት ለማን ጠቀመ ወይንም እድገቱ ለማነው? የሚለውን መሰረታዊ ጥያቄ ለመመለስ ቀላል ነው። ከሁሉም በላይ የእድገቱ ተጠቃሚዎች የገዢው ፓርቲ ባለሥልጣናትና ቤተሰቦቻቸው ናቸው። ተለጣፊ ተጠቃሚዎችም አሉ። ይኼ የወደፊት አደጋን ያዘለ የእድገት ሂደት ከአሁኑ ካልተቀረፈ ያለው ስርዓት ወለድ የሆነ ህብረተሰቡን በማናጋት ላይ ያለው የብሄር፤ ብሄረሰብና ኃይማኖት ልዩነት እየከረረ መሄዱ የማይቀር ነው። ገቢና ኃብት በጥቂቶች ከተከማቸ (Concentration of incomes and wealth in a few families) አብዛኛው ህዝብ መደህየቱ የማይቀር ነው። የቁም ተመልካች ይሆናል። እነዚህ ሳያመርቱና ለሌሎች የስራ እድል ሳይፈጥሩ በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ታይቶ የማይታወቅ የድሎት ኑሮ የሚኖሩ የባለሥልጣናት ግለሰቦችና ቤተሰቦች ያላሰቡበት አደጋ እንደሚከተለው ነው።

ማንኛውም ኢትዮጵያዊ በአገሩ በክብር የመኖር መብት አለው። ይኼ ክብር ስራ ከማግኘት፤ በቂ ምግብ በልቶ ከማደር፤ የጤና፤ የትምኅርት፤ የመጸዳጃ፤ የንፁህ ውሃና የመጠለያ አገልግሎት ከማግኘት ጋር የተያያዘ ነው። ነጻነት፤ ፍትህና ሰብአዊ መብቶች ትርጉም የሚኖራቸው እነዚህ ሁኔታዎች ሲሟሉ፤ በምድር ላይ ሲታዩ፤ ሲዳሰሱና ስኬታማ ሲሆኑ ነው። በብሄራዊ ደረጃ ጠንካራ የሆነ የማህበረሰብ ትሥስር (Social Cohesion) ሊፈጠር የሚችለው የእድገቱ ውጤት ለአብዛኛው ህዝብ ሲደርስ ነው። የእድገቱ ትኩረት ለጥቂቶች የድሎት ኑሮ ከሆነ ዘላቂነትና ፍትሃዊነት ያለው የእድገት መሰረት ስኬታማ ሊሆን አይችልም። ዛሬ በግብጽ (ሳይናይ)፤ በሊቢያ፤ በሶሪያ፤ በአፍጋኒስታን፤ በኢራክ፤ በየመን፤ በናይጀሪያ፤ በማሊና በሌሎች አገሮች የምናየው ቀውስ የፍትሃዊ እድገት አለመኖር ውጤት ነው የሚሉ ብዙ ምሁራንና ባለሞያዎች አሉ። ከእነዚህ መካከል በገቢና ኑሮና መዛባት ወይንም ኢፍትሃዊነትና በሽብርተኛነት መካከል ያለውን ቀጥተኛ ግንኙነት ጥልቀት ባለው ጥናትና ምርምር ያቀረበው የፈረንሳዊው ኢኮኖሚስት ቶማስ ፒኬቲ በመካከለኛው ምስራቅ ለሽብርተኞች ቀስቃሽና ሰብሳቢ የሆነው ዋና ምክንያት የገቢና የኑሮ ልዩነት ነው ይላል። "There are regimes that are militarily and politically supported by Western powers, all too happy to get some crumbs to fund their soccer clubs or sell some weapons. No wonder our lessons in social **justice and democracy** find little welcome among Middle Eastern youth."

ፕሬዝደንት ኦባማ ኢትዮጵያን ሲጎበኙ ስለ ፍትህ፤ ስለ ነጻነት፤ ስለ ተሳትፎ፤ ስለ ዲሞክራሲ፤ ስለ ሙስና ወዘተ ተናግረው ነበር። "እኛ ከኢትዮጵያ መንግሥት ባለሥልጣናት ጋር ግልጽነት ያለው (frank) ውይይት አድርገናል" ብለው ነበር። ከዚያ ወዲህ ምን ለውጥ ተደረገ ብየ እራሴን ስጠይቅ፤ ሁኔታዎች ተባባሱ እንጅ ተሻሻሉ ለማለት የሚያስችለኝ መረጃ አላገኘሁም። ለደህንነት፤ ለመከላከያና ሌላ የሚሰጠው የአሜሪካ እርዳታ ቀጥሏል። የማህበራዊ ደህንነት በመሻሻል ፋንታ እየተባባሰ ሂዷል። የህዝባዊ ዓመጽ፤ የሽብርተኛነት፤ የተገንጣይነት፤ የስደት፤ የተስፋ መቁረጥ ወዘተ መንስኤዎች በአብዛኛው የኢኮኖሚ ችግሮች ናቸው-- የስራ እድል አለመኖር፤ የገቢ ዝቅተኛነት አስጊ የሆነ የገቢና የኑሮ ልዩነት፤ የአፈና፤ የረሃብና ተመሳሳይ ማህበረሰባዊ ችግሮች። የምእራብ አገሮችና የውጭ ኢንቬስተሮች እነዚህን የአገዛዝ ሁኔታዎች የማሻሻል ግዴታ አለብን ብለው አያውቁም። አትራፊዎች ትርፍን፤ የአገሮቻቸውን ጥቅም አስከባሪዎች ታማኝና ታዛዢ የሆኑ ባለሥልጣናትን ይንከባከባሉ። ኪራይ ሰብሳቢዎች በዚህ ይከብራሉ። የገቢና የኃብት ክምችትን እንደ ልማት ያዩታል። የፒኬቲ ጥናት ያሳየው ባጠናቸው አገሮች ሁሉ "Those economic conditions (inequality, depravation, moral decay, decadence) have

become justifications for jihadists (terrorists). ይኼን ፅንሰ ሃሳብ ልንቀበል ላንቀበል እንችላለን። የማይካደው በኪራይ ሰብሳቢነት፤ በጉቦ፤ በሙስናና በጎሳዊ አድልወ የተበከለ አገዛዝ የራሱን መጥፊያ እንደሚፈጥር አይካድም።

በአጭሩ፤ በመካከለኛው ምስራቅና በሰሜን አፍሪካ የተከሰተው ሁኔታ በኢትዮጵያም ሊከሰት ይችላል። የተዛባ የገቢ፤ የኃብትና የኑሮ ስርጭት ሽብርተኛነትን ያጠናክራል። ሽብርተኛነትን ከድህነት፤ ከረሃብ፤ ከኢፍትሃዊ የገቢና የኃብት ስርጭት ለይቶ ማየት አደገኛ ነው። ግብጽና ኢትዮጵያ የሚከተሉት የፀረ-ሽብርተኛነት ዘመቻ አግባብ ያለው ቢሆንም የችግሮቹን መንስኤ ፍጹም አልነካቸውም። ሁለቱም አምባገነን ገገሮች በአገር ውስጥ ሆነ ከአገር ውጭ፤ ትችት የሚያቀቡባቸውን ሁሉ በጠላትነት ያያሉ። ልዩነት ለማስተናገድ አልቻሉም። ይኼ ብቻ ችግሩን እያሰፋው ይሄዳል። የገቢ፤ የኃብትና የድሎት ኑሮ **<u>ለጥቂቶች ብቻ ሲሆን ከእሳቱ ላይ ቤንዚን ማፍሰስ</u>** ይሆናል። በእኔ ግምት በኢትዮጵያና በሌሎች አገሮች ድህነት፤ ረሃብ፤ የኑሮ ውድነት፤ ኪራይ ሰብሳቢነት፤ ስራ አጥነት፤ ስደት፤ **<u>የገቢና የኃብት ልዩነት፤</u>** የአካባቢ ሁከት፤ ሙስናና ሌሎች ህብረተሰብን አድካሚ ችግሮች የተከሰቱትና የሚከሰቱት፤ በአብዛኛው፤ በአምባገነናዊ አገዛዝ ምክንያት ነው። የኢትዮጵያ መሰረታዊ ችግር ይኼው ነው። ቀረብ ብሎ ለተመለከተው ለኢትዮጵያ ሕዝብ በአጭር ጊዜ ውስጥ ሊፈታ የማይችል የሚመስለው ተግዳሮት የልዩ ልዩ የጥቅም ሰንሰለቶች ተቋማዊ በሆነ መንገድ መፈጠራቸው ነው። ሁለት ምሳሌዎችን አቀርባለሁ።

አንድ፤ የህወሓት መሪዎች ሆነ ብለው የመሰረቱት የፖለቲካ ስልጣን መረብ የተያያዘና የተቆላለፈ የፋይናንስ፤ የመሬት፤ የግንባታ፤ የምርት፤ የንግድ፤ የውጭ ምንዛሬ ወዘተ የጥቅም መረብ ዘርግቷል። የፖለቲካው ስልጣን የኢኮኖሚ የበላይነትን ወልዷል ማለት ነው። የፖለቲካ ስልጣን ቁይታ ስኬታማነት ከስለላና ከመከላከያ ኃይል የበላይነት ጋር የተያያዘ መሆኑን በግብጽ፤ በሊቢያ፤ በሶሪያ፤ በችሌ፤ በቻይና፤ በፊሊፒንስ ወዘተ አይተናል። ይኼ የበላይነት ቆይታ ሊኖረው የሚችለው ቀስ በቀስ ቁልፍ የሆኑ የስለላ፤ የፖሊስ፤ የመከላከያና ሌሎች ፖሊሲ የሚያወጡ፤ ገቢ የሚሰበስቡ፤ የስራ ፈቃድ የሚሰጡ፤ የኢንቬስትመንት ውሳኔ የሚያደርጉ፤ የባጀት ፈሰስ የሚወስኑ፤ የተፈጥሮ ኃብት ስርጭትን አስተዳደር የሚበይኑ ወዘተ ኃይሎች የጥቅም ተካፋይ ሲሆኑ ነው። ኃብታም ሲሆኑ ስርዓቱ እንዳይፈርስ ተገን ይሆናሉ። የመከላከያ የበላዮችን ምሳሌ እንይ። M&G African Writer, November 26, 2015: "**Military Inc: African Armies are big players in economies—with Ethiopia, Egypt top of the list,**" ከዚህ በፊት ባቀርብኳቸው ሃተታዎች የኢትዮጵያ ገዢ ፓርቲ፤ በተለይ ህወሓት፤ በኢኮኖሚው የበላይነት ከፍተኛውን ደረጃ እንደያዘ አሳይቻለሁ። ፓርቲውን ከመንግሥትና ከኢኮኖሚው እንቅስቃሴ ለመለየት አይቻልም። በሁሉም የስራ ዘርፎች ተሰራጭቷል፤ ስር ሰዷል።

የኢትዮጵያ የመከላከያ ኃይል ከፍተኛ ባለሥልጣናት በአዲስ አበባና በሌሎች ከተሞች ከፍተኛ ኃብትና ጥሪት እንደሰበሰቡ ብዙ ማስረጃዎች ቀርበዋል። እነዚህ ከፍተኛ ባለሥልጣናት ከሚያገኙት ደሞዝና ሌላ ክፍያ በላይ የሚያንቀሳቅሱት ግዙፍ መዋእለንዋይ እንዳለ ይነገራል። ከላይ የጠቀስኩት ዘገባ እንደሚለው፤ የኢትዮጵያው መከላከያ ኃይል ድርጅት Metals and Engineering Corporation (METEC) በአፍሪካ አህጉር አምስት ከፍተኛ ሚና ያላቸው የመከላከያ ተቋሞች መካከል አንዱ መሆኑን ዘግቦ **<u>የዛሬ አምስት ዓመት</u>** የተቋቋመው ይኼ ህወሓት በበላይነት የሚመራው የኢኮኖሚ ተቆጣጣሪና አንቀሳቃሽ ድርጅት **<u>አስራ አምስት</u>** የተለያዩ የምርትና የአገልግሎት ድርጅቶች ባለቤት ነው፤ አምሳ ፋብሪካዎች በባለቤትነት ይዟል ይላል። ኤፎርት የተባለውን ህወሓት ያቋቋመውን አትራፊ ድርጅት ያስታውሰኛል። "It is essentially a conglomerate estimated to be running well **<u>over 50 factories</u>** and reporting directly to the country's top leadership."

ይኼ ግዙፍ የኢኮኖሚና የፋይናንስ ተቋም ምን ያመርታል? ማን በባለቤትነት ይዞታል? ምን ጫና ያደርጋል? ከመሰረታዊው አገርን ከውጭ ጠላቶች ከመከላከል ሚናው በምን ይለያል? ተቋሙ በኢንዱስትሪ ምርቶች፤ ለምሳሌ ስኳር፤ በውሃ የኤሌክትሪክ ኃይል አቅርቦት ስራ፤ መኪናዎችን በመገጣጠም፤ በምርምርና በሳይንሳዊ ጥናት፤ በመሃንዲስነትና በግንባታ፤ በንግድ ወዘተ ተግባሮች ተሰማርቷል። "የኢትዮጵያ መንግሥት ብቸኛው የስኳር አምራች ነው" ሲባል፤ የግል ክፍሉስ የት ሄደ? ለምን ታፈነ? መንግሥት ሲባል ማንን ይወክላል? የሚሉት የኢኮኖሚና የባለቤትነት ጥያቄዎች አግባብ አላቸው። መልሱን ለአንባቢ እተወዋለሁ።

በእኔ ግምት የመከላከያ ኃይሉ የሚታይና የሚዳሰስ ጠቃሚም ጎጅም ሚና አለው። በጠቃሚነቱ ኢትዮጵያ በመሳሪያ ራሷን እንድትችል የምርት ኃይሏን ማጠናከሩ ወሳኝና ጠቃሚ የሆነ ሚና ነው። የአፄ ኃይለ ሥላሴና የደርግ መንግሥታትም ባለቸው የተወሰነ የገንዘብ አቅም ኢትዮጵያ በጦር መሳሪያዎች ራሷን እንድትችል ጥረት አድርገው ነበር። የአሁኑን የመከላከያ ኃይል ካለፉት የሚለየው ግዙፍ የሆነ ካፒታል ያለው መሆኑ፤ የግለሰቡ ክፍል ሊሰራቸው በሚችለው የምርት ክፍሎች መሰራጨቱና ለጥቂት የበላዮች ግዙፍ የሆነ ገቢና ኃብት ማስገኘቱ ነው። ለምሳሌ፤ በሌሎች አገር እንደሆነው የግል ክፍሉ

ስኳር ለማምረት ይችላል። በግንባታ ስራዎች ሊሳተፍ ይችላል። ገዢው ፓርቲ ብቸኛው የስኳር አምራችና ቸርቻሪ የሆነበት ምክንያት ለአገሪቷን ለህብረተሰቡ ጥቅም ነው ወይንስ ለግልና ለቡድን ጥቅም?

የተሃድሶ ግድብ ስራ የሁሉም ኢትዮጵያዊያን ኃላፊነትና ስራ መሆኑን ከዚህ በፊት ስለጉዳዩ በጻፍኳቸው ሃተታዎች አቅርቤአለሁ። የኢትዮጵያ መብራት ኃይል ወይንም ኮርፖሬሽን ግድቡን በመስራት ሚና አለው። ሆኖም፤ አንድ ግዙፍ ግድብ ወይንም ሌላ ግንባታ ሲደረግ የኢትዮጵያ የግል ክፍል፤ ግለሰቦችም ሆኑ ድርጅቶች፤ በአገር ቤት ያሉ ሆኑ በውጭ እንዲሳተፉ መጋበዝና አቅም እንዲኖራቸው ድጋፍ መስጠት የመንግሥት ሚና ነው። የመከላከያ ኃይሉን በተናጠል ከፍተኛ ሚና መስጠት አከራካሪ የእድገት ሂደት ነው። የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ የሚሊታሪ ኢኮኖሚ እንዲሆን መደረጉ ሁሉን አሳታፊ የሆነ የግል ኢኮኖሚ እንዳይመሰረት ማነቆ ይሆናል። የገቢና ኃብት ስርጭቱን ኢ-ፍትሃዊነት ያባብሰዋል። የመከላከያ ኃይሉ ብሄራዊ መሆኑ ቀርቶ ወገናዊና ጎሳዊ እንዲሆን ያጠናክረዋል። ምክንያቱም፤ በግብጽና ሌሎች አገሮች እንደታየው፤ ኢኮኖሚው ሚሊታራዊ ከሆነ ከፖለቲካው ጋር ቀጥተኛ ግንኙነቱ ተጠናክሮ ዲሞክራሳዊ አገዛዝ እና መልካም አስተዳደር እንዳይመሰረት ማነቆ ይሆናል። ይኼን ያባባሰው ገዢው ፓርቲ የግሉ ክፍሉ ወሳኝ የሆነ ሚና እንዳይኖረው የፖሊስ፤ የአመራር፤ የአስተዳደር ወዘተ ጫና አድርጓል፤ እያደረገ ነው። ማን የበላይ፤ ማን የበታች እንደሚሆን ይወስናል። ከላይ የጠቀስኳቸው ምሳሌዎች የሚያሳዩት፤ ገዢው ፓርቲ የግሉ ክፍል እንዲጠናከር በማድረግ ፋንታ ፓርቲውንና የሚቆጣጠረውን የመከላከያ ኃይል አምራችና ነጋዴ አድርጎታል። ይኼ የሚያስታውሰኝ የሞባረክን ግብጽ ነው።

በማንኛውም አገር የስራ ክፍፍል የተለመደ ነው። የመከላከያ ኃይሉ በዋናው አገርን የመታደግ ሚናው ዝነኛ የሆነ ባህልና ታሪክ አለው። በሶስቱም መንግሥታት የኢትዮጵያ የመከላከያ ኃይል በዓለም ዝናን ያስገኘ (ኮሪያና ኮንጎ፤ አሁን ዳርፉር ወዘተ) የሚያኮራ አስተዋፆ አድርጓል፤ ቀልጣፋና አገር ወዳድ ኃይል ነበር፤ አሁንም ነው። ሚናውን አስተማማኝ ለማድረግ የጦር መሳሪያዎችን ቢሰራ፤ ቢያሻሽልና የተረፈውን ለውጭ ገበያ ቢያቀርብ ያስመሰግናል እንጅ እያስነቀፍም። ከግሉ ክፍል ጋር እየተወዳደረ **__የግሉን ክፍል ጫጬት__** የሚያደርግ ከሆነ ግን ዞሮ ዞሮ የእድገት ማነቆ መሆኑ አይቀርም። ጎሳዊነት ተቋማዊ ሆኖ እንዲቆይ ያደርጋል። የምርት ኃይሎች የአገርን ኢኮኖሚ ሚሊታራዊና ጎሳዊ በማድረግ ፍላጎትን በተመጣጣኝ ደረጃ ሲያሟሉ አላየሁም። ይኼን ሁኔታ ከሌሎች የገዢው ፓርቲና መንግሥት ሚናዎች ለይቶ ለማየት አይቻልም። በሁሉም ዘርፎች ቁጥጥሩ ተቋማዊ ሆኗል። Aaron Maasho, Rueters, November 24, 2015 ዓለም ባንክን ጠቅሶ ኢትዮጵያ የመሰረተ ልማት ተግባሮቿን ስኬታማ ለማድረግ በፓርቲውና በመንግሥት የበላይነት መመካቷ "መቆም አለበት"፤ ቢያንስ በመሰረተ ልማት የሚካሄደው የኢንቬስትመንት ስርጭት የግል ክፍሉን አሳታፊ መሆን አለበት ብሏል። ከላይ እንዳቀርብኩት፤ የግል ክፍሉ ሚና ጫጬት የሆነበት ምክንያት፤ የገዢው ፓርቲ ተቋሞች በአገር ስም አንበሳውን ሚና ስለሚጫወቱ ነው። የመከላከያው ተሳትፎ ሁኔታውን አባብሶታል። **__ባንኮቹ ከሚያበድሩት 27 በመቶውን__** ለገዢው ፓርቲ (በመንግሥት ስም) ማበደር ግዴታ ሆኖባቸው ቆይቷል። መከላከያው በሺሚያው ይሳተፍ አይሳተፍ ግልፅነት የለም።

አመራሩ በግሉ ክፍል እንቅስቃሴ ላይ ከፍተኛ ጫና አስከትሏል። አንድ ግለሰብ ለመበደር ያለው እድል የመነመነ ነው፤ ከባንክ ተበድሮ አዲስ ተቋም ለመመስረት አልተቻለም። በዓለም ባንክ ዘገባና ማሾ እንዳለው፤ "Continued infrastructure development remains one of Ethiopia's best strategies to sustain growth, but the current financing model is not sustainable." ዓለም ባንክ የተለመድውን መፍትሄ፤ ተጨማሪ ታክስ፤ የኤሌክትሪክ ዋጋ ጭማሪ ወዘተ ያቀርባል። ችግሩ መንግሥት የሚገባውንም ቀረጥ ለመሰብሰብ አልቻለም። ገቢ ዝቅተኛ፤ ዋጋ ሰማይ ጠቀስ ከሆነ ቁጠባ አይቻልም። ያላቸው ግለሰቦች ኃብታቸውን የሚያውሉት ለፍጆትና ለድሎት ነው---የድሎት መኪና፤ ቪላ፤ የዱባይ ሽርሽር ወዘተ። ለነገ የሚል ትውልድ የለም።

ባንኩ መሰረታዊ የአገዛዝ ችግሩን ፈጽሞ አይነካም። የግሉ ክፍል አግባብ ያለው ሚና መጫወት አለበት የሚለውን እጋራለሁ። ሌላው ባንኩ ምንም የማይነካው ባለቤትነትን ነው። የኢትዮጵያ ዘመናዊ **__ኢኮኖሚ በጥቂቶች የአገር ውስጥና የውጭ ባለቤትነት የተያዘ ነው። የመከላከያ ኃይሉን ጥሪቶች ቀረብ ብለን ብንመረምር የበላዮቹ የአንድ ብሄረሰብ፤__** ማለትም የህወሓት አባላት ናቸው። ይኼ በይፋ የሚታይ ወይንም አይን ያወጣ የመከላከያው ክፍል የበላዮች የመሳሪያና የገንዘብ አቅም ያለው ተቋም የበላዮቹን አክብሯል። አዲስ የኃብታም መደብ ተፈጥሯል የሚለውን ጽንሰ ሃሳብ ከተቀበልን፤ እኔ እቀበላለሁ፤ የመከላከያ ኃይሉ ከፍተኛ አባላት ቤተሰቦች የገቢ፤ የኃብትና የምርት ኃይሎች ክምችት (Concentration of real assets) አላቸው። በገዢው ፓርቲና በመከላከያው መካከል የጥቅም ትሥስር ተፈጥሯል። ዓለም ባንክ ለውጥ (essential financial reform) ያስፈልጋል ቢልም፤ ውጤቱ እንደ ሙስናው ጥናት ይሆናል። ምንም ለውጥ አይቻልም፤ አዲስ ተጠቃሚዎች ለውጥ አይፈቅዱም። ዓለም ባንክ እንደተለመደው የጻፈውን ወደ ስራ አይለውጥም።

ሁለት፤ የሮይተሩ ማሾ **“Ethiopian entrepreneurs struggle as command economy soars,” November 18, 2015,** በተባለው ሃተታው የግሉን ክፍል የፖሊሲና መዋቅራዊ ችግር በሚገባ አቅርቦታል። ከላይ እንዳሳየሁት፤ የግል ክፍሉ በእየአቅጣጫው መሰናክሎች ገጥመውታል። ለምሳሌ፤ ዘመናዊ መገናኛን በሚመለከት ኢትዮጵያ ከሩዋንዳ፤ ከኬንያ፤ ከፈረሰችው ሶማሊያ ወዘተ ጋር ለመወዳደር አልቻለችም። ገዢው ፓርቲ ህወሓት በበላይነት የሚቆጣጠረው የኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን ድርጅት ኢንንተርኔት፤ ሞባይልና ሌሎች የማህበረሰብ መገናኛዎችንና ስራ ፈጣሪ የሆኑትን መገናኛዎች አፍኗቸዋል። ግለሰቦች ትችት እንዳያቀርቡ ይፈራሉ፤ ትችት ማቅረብ የባሰ ችግር ያስከትላል፤ ያሳስራል፤ የግል ኃብትን ያስቀማል ወዘተ። “የመገናኛ መሳሪያ መሰረት ያደረገ” ቴክኖሎጅ፤ የምርትና የአገልግሎት ተቋም ለመንቀሳቀስ አይችልም። ማሾ አንድ ግለሰብ ጠቅሶ “Ethiopia is leaving out a huge talent-based opportunity” ይላል። የኬንያና የሯአንዳ ወጣቶች እድለኞች ናቸው። መንግሥቶቻቸው ዘመናዊ የመገናኛ ቴክኖሎጅ ተጠቅመው ምርት እንዲያመርቱ፤ አገልግሎት እንዲሰጡ፤ እውቅት እንዲያሰራጩ፤ ስልጠና እንዲሰጡ፤ ወገኖቻቸውን እንዲቀጥሩ፤ እነደልባቸው እንዲንቀሳቀሱና እንዲሰሩ ያልተቆጠበ ድጋፍ ይሰጣሉ። በኢትዮጵያ የተለያዩ የአስተዳደርና የአመራር ማነቆዎች የተለመዱ ናቸው። ባንኮች ለወጣቶች ለማበደር እንዳይችሉ፤ ፓርቲውና የሚቆጣጠረው መንግሥት ጫና ያደርጋል፤ ለብድር ይሻማል። አቅም ስላለው የግሉን ክፍል በረባ ባልረባው ያፍነዋል፤ ያጉላላዋል። በኬንያ ሁለት ሶስተኛው ሕዝብ የኢንተርኔት ግንኙነት አለው፤ ኬንያዊያን ገንዘብ በሞባየል ያስተላልፋሉ። ዱሮ የባንክ ሂሳብ የሌላቸው M-Pesa የተባለ በሞባይል የተደገፈ መሳሪያ ተጠቅመው የባንክ አገልግሎት በመላው ኬንያ አገልግሎት ያገኛሉ። ገበሬውም፤ ዘላኑም ይጠቀምበታል። በኢትዮጵያ ስራ ለመስራት ኪስን በብር ሞልቶ መሄድ አስፈላጊ ነው። የካሽ ኢኮኖሚን ለመቆጣጠር አይቻልም። “Mobile users complain that even basic telephone coverage is poor and Internet speeds are sluggish in the capital.” ቴሌኮም እንደ ላም የሚታለብ በ2014/15 ብር 21.5 ቢሊየን ገቢ ያስገኘ ድርጅት ነው። የግል ተወዳዳሪ እንዲጎለምስ አይፈልግም። ሌላም ጥቅም አለው፤ ቁጥጥር ይባላል።

ገዢው ፓርቲ የሚለው ተጻራሪ ሃሳብ አለ። ይኼውም የግሉ ክፍል የሞባይል ስርጭት ስኬታማ ለማድረግ አይችልም የሚል ነው። ኬንያና የፈራረሰችው ሶማሊያ ያደረገችውን ኢትዮጵያዊያን ለማድረግ የማይችሉበት ምክንያት ግልጽ ሊሆንልኝ አልቻለም። የነፍስ ወከፍ ገቢ ዝቅተኛ ስለሆነ ነው የሚለው አከራካሪ ሆኖ አገኘዋለሁ። በባንግላደሽና በሕንድ አገር ፍጹም ድሃ የነበሩ የገጠር ዜጎች በሞባይል ስርጭት ተጠቅመዋል። ኬንያና ርዋንዳ ፍጹም ድሃ ነበሩ፤ ውድድር ያለበት ኢኮኖሚ ስለፈጠሩ፤ መካከለኛው መደባቸው ከኢትዮጵያ የበለጠ ሆኗል። ስለሆነም፤ አግባብ ያለው፤ ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው ኢትዮጲያዊያን በዝቅተኛ ዋጋ ሊገዙት የሚችሉትን ቴክኖሎጅ ማቅረብ ነው። ወጣቱ ትውልድ በቴክኖሎጅው እንዲጠቅም ማነቆዎችን ማስወገድ ነው። ድሃው ሁልጊዜም ድሃ ስለሆነ እንደ ደኼየ ይቆይ የሚል የእድገት መርህ ድህነትንና ኋላ ቀርነትን እንደ ልምድ አድርጎ እድገቱ በጥቂት ቤተሰቦች ዙሪያ (በውደት) ኢንዲሽከረከር አድርጎታል። የእድገት ዋና መስፈርት ድሃው ህዝብ ከድህነቱ ነጻ እንዲወጣ ነው። የዓለም ባንኩ ኢኮኖሚስት ላርስ ክርስቲያን ሞለር ያለውን እጋራለሁ። “International experience would suggest that if you were to open (the economy and the market), you would get lower prices, higher quality and better coverage.” ክፍት ይሁን ሲባል የውጭ ኢንቬስተሮች ኢትዮጵያን በባሰ ሁኔታ ይውረሯት ማለት አይደለም። ኢትዮጵያዊያን የማምረት ኃይሉ ሞተር ይሁኑ፤ የምርታቸው ውጤት ባለቤት ይሁኑ ማለት ነው። ይኼ ስኬታማ ሊሆን የሚችለው ገዢው ቡድን የቀድሞዎቹን ፌውዳል የመሬት ባላባቶች የሚመስል ትሥስር ትቶ ለግሉ ክፍል አድልዎ ሲያደርግ፤ ከኪራይ ሰብሳቢነት ራሱን ሲያጸዳ፤ ግልጽነትና ተወዳዳሪነት ያለው የኢኮኖሚ መሰረት ለመጣል ሲደፍር ነው። ደፋርነት መሳሪያ ይዞ ማስፈራራት አይደለም። ደፋርነት ለህዝብ ጥቅም መቆም፤ ህዝብን ማገልገል፤ የአገርን ዳር ድንበት አለማስነካት፤ ለፍትሃዊ ለውጥ አድልወ ማድረግ ነው።

ይኼ ምኞት ይመስላል። በእኔ ግምት የገቢና የኃብቱ ስርጭት የኢትዮጵያን ሕዝብ ስርጭት የሚወክል ካልሆነ የእድገት መዛባት ብቻ ሳሆን የማህበረሰብ ቀውስ (Social Crisis) መከሰቱ አይቀርም። በብሄር፤ ብሄረሰብ ጭቆና አመካኝተው ራሳቸውን እንደ ዱሮዎቹ መሳፍንትና ፌውዳሎች “እኔ ከሞትኩ ሰርዶ አይብቀል” ካሉ አገሪቱ በኪራይ ሰብሳቢነትና በአቋራጭ የመክበር መርህ ትደማለች፤ ድህነት ጥልቀትና ስፋት ይይዛል፤ የድርቅ ረሃብ አይፈታም። በመልካም አስተዳደር ዙሪያ በተደረገው ውይይት እንደቀረበው፤ አብዛኛው የኢትዮጵያ የከተማና የገጠር ነዋሪ በመሬት ነጠቃ፤ ዘረፋ እና ቅርሚት ኪራይ ሰብሳቢዎች እየደማና እየደቀቀ ነው። ጥናቶችና ታዛቢዎች የሚሉት 76 በመቶ የሚሆነው ኪራይ ሰብሳቢነትና በፍጥነት ኃብታምነት የሚካሄደው በመሬት ንግድ ዙሪያ ነው። የመሬት ንግድ ሲጦፍ የሚጎዳው ከፍተኛ ገቢ የሌለው ክፍል ነው። ይኼ ጎሳና ኃይማኖት ወይንም ጾታ አይለይም። ከእድገቱ ማን ተጠቀመ? የሚለው ጥያቄ በአብዛኛው ከመሬት ሽያጭ፤ ኪራይና ንግድ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት አለው። አንዳንድ ተመልካቾች የኢትዮጵያን እድገት ፈጣንነት ተቀብለው ምሳሌዎች **<u>ሲሰጡ በ2013፣ 2,700 ሚሊየኔሮች</u>** ተፈጥረዋል ይላሉ። በአፍሪካ የመጀመሪያውን ደረጃ የያዘ የገቢና የኃብት ክምችት ተፈጠረ ማለት ነው። ሊሆን ይችላል። በራሱ ጥረት ሰርቶና ፈጥሮ ሚሊየኔር መሆን አግባብ አለው። መልስ ያላገኘው ምን

አምርተውና ምን ለአገር ውስጥና ለውጭ ገበያ አቅርበው ወደ ሚሊየኔርነት ተሸጋገሩ? የሚለው ነው። የቤት ግንባታን በአጭሩ እንይ።

በእቅድ የሚካሄድና ሚዛናዊ የሆነ የከተማ ስፋትና ልማት አግባብ አለው፤ የትም አገር ይሆናል። ዛሬ አከራካሪ የሆነውን የአዲስ አበባ የመሬት ነጠቃ፤ ጎጆ ያላቸውን አስወግዶ በምትካቸው ቪላዎች መስራት፤ ገበሬዎችን ከመሬታቸው ልቀቁ ብሎ የአዲስ ኃብታሞች መንደሮች መስራት ወዘተ ያስከተለው የማህበረሰብ ቀውስ እንዳለ ብዙም **አንነጋገርበትም።** ይኽ የፖለቲካ ጨዋነት ወደፊት ሊከሰቱ የሚችሉ ችግሮችን አስቀድሞ ለማስወገድ ማነቆ ሆኗል። ቪላዎች ሲሰሩ ከአገሪቱ የማምረት አቅም በላይ የሚፈጅ ግብአት ከውጭ ተሸምቶ በውጭ ምንዛሬ ይከፈላል። ባይሆን አዲሶቹ ሚሊየኔሮች **ከውጭ ከቻይና የሚገዛውን ብረታ ብረት፤ መስኮት፤ በርና ሌላ ለዘመናዊ ቤት አስፈላጊ እቃ** በአገር ቢያመርቱ የውጭ ምንዛሬ ይቆጠባል፤ የስራ እድል ይፈጠራል፤ ራስን የመቻል ባህል ስር ይሰዳል፤ ዋጋ ይቀንሳል፤ ዝቅተኛ ገቢ ያለው ሰርቶ አደር ቤት ለመስራት ይችላል ወዘተ። በቅርቡ በአዲስ አበባ ዙሪያ የሚሰራ የአዲስ ቪላ ዋጋ በዓለም ድሃ፤ ኋላ ቀር፤ ረሃብተኛና የምግብ ጥገኛ በሆነችው ኢትዮጵያ "እንዴት ይቻላል?" የሚል ጥያቄን አስከተለብኝ። በአካባቢው የሚኖሩ ዜጎች ሚና አላቸው ወይንስ የላቸውም የሚለውም አግባብ አለው። የድሎት ቪላ ስራዎችን ስመለከት፤ በአማካይ፤ አንድ ቪላ **$330,000** ወይንም **ብር 6,600,000** ያወጣል። ከተራው ሰርቶ አደር አቅም አንጻር ሳየው ለፌደራሉ መንግሥት የሚሰራ ወይንም የምትሰራ፤ ከፍተኛ ትምኅርት የጨረሰ ወይንም የጨረሰች የኮሌጅ አስተማሪ፤ የራሱ ወይንም የራሷ ተቋም ያላት ግለሰብ ይኼን ዋጋ እንዴት ትችለዋለች? የዚህ እድል ያላቸው ግለሰቦች የውጭ ምንዛሪውን ከየት ያመጡታል? ወዘተ። የእድገት እንቆቅልሽና አዲስ ትርጉም ያስፈልጋል የሚያስብለው ይኼም ጭምር ነው።

በሌሎች የአገዛዝና የአመራር ችግር ባለቸው አገሮችም ይኼ አስጊ የሆነ የተዛባ ገቢና የተዛባ የኑሮ ሁኔታ ይታያል፤ እንደዚህ ግን ጎልቶ አላየሁትም። ቬኔዙኤላ ከቻቬዝ በፊት፤ ኩባ ከአብዮቱ በፊት። የገቢውና የኑሮው ልዩነት የመካለለኛውን መደብ ስፋት ሳይሆን የሚያሳየው የጠበበ መሆኑን ነው። ኢትዮጵያ ይኼን እየባሰ ሊሄድ የሚችል የገቢና የኑሮ ልዩነት እንዴት እንደምትወጣው መልስ የለኝም። ሆኖም የኢኮኖሚው አመራር ጉድለት እንዳለው ለመናገር እችላለሁ። ዙሮ ዙሮ የዚህ አይነቱ የገቢና የኑሮ ልዩነት ሊፈጠር የቻለው በአገዛዙ ነው። በቅርቡ የህወሓት ደጋፊ በሆነው አይጋ ፎረም እንደ መስቀል ወፍ ብቅ ያለ በማስረጃ የተደገፈ ትንተናና ትችት አንድ ወዳጀ ሰጥቶኝ አንብቤ ነበር። በአበበ ሃይለ የተጻፈው አርእስት ይሰባል። **"ልብ ያለው ልብ ይበል"** እንዲህ ሲል ይጀምራል። "በአብዛኛው ጊዜ እንደሚስተዋለው ከፍተኛ የፓርቲ ወይንም የመንግሥት ባለሥልጣናት ስለ አንድ ችግር ለውይይት ሲቀመጡ ራሳቸውን እንደ ንጹህ በማስቀመጥ ጣታቸውን የሚቀስሩት ከነሱ በታች በየርከኑ ባሉ ባለሥልጣናት ላይ ነው። እንደዚህ አይነት አካሄድ በየርከኑ ያለው የአመራር አካል ስለሚጠቀምበት ችግሩ የት ላይ፤ ማን ጋር መሆኑ ግራ በሚያጋባ መልኩ ለተወሰነ ጊዜ ሞቅ ሞቅ ብሎ የሚጠፋ ይሆናል።" ትክክል ነው። ባለቤትነትና ሃላፊነት የሌለበት የአገዛዝ ስርአት የሚሰራው በዚህ መልክ ነው። ተጠቃሚው ከላይ ወደታች የተያያዘና የተሳሰረ ስለሆነ ግልፅነት፤ ተጠሪነትና ሃላፊነት ተደብቀውና ተሸፍነው ነው የሚካሄዱት። ማን ይጎዳል? ብየ ስጠይቅ አብዛኛው ከጥቅሙ ውጭ የሚኖረው ሕዝብ ነው። ግልጽነት፤ ሃላፊነት፤ ተጠሪነትና የመንግሥት ባለቤትነት ከሌለ ኪራይ ሰብሳቢነትና ሙስና ሊወገዱ አይችሉም። ክትትል ተደርጎ ለፍርድ የሚቀርቡት ዝቅተኛ ወይንም በፖለቲካ የሚፈለጉ ሙሰኞች ናቸው። ቁንጮው አይነካም።

የኢትዮጵያ ኪራይ ሰብሳቢነት ባህል በቡድን ትሥስር የተደገፈ ነው። አንዱ ለሌላው ጠበቃ ይሆናል። የተቋም ሃላፊዎች አይተው እንዳላዩ የሚያደርግ አሰራር ነው። ፀሃፊው እንዲህ ይላል። "ሁሉም ኪራይ ሰብሳቢ ባለሥልጣን በፍርድ ቤት ጠረጴዛ ይለፍ ከተባለ ጉዳዩ የባሰ ውስብስብ ሊያደርገው ካልሆነ መፍትሄ የማይገኝለት ይሆናል። በስልጣን የሚባልግ ሁሉ ከተጠያቂነት ለማምለጥ ሕጋዊነትን ሽፋን እያደረገ ስለሚንቀሳቀስ ተጨባጭ ማስረጃ እስኪገኝ የሚጠበቅ ከሆነ ፋይዳ ያለው ስራ ሳይሰራ ጡረታ የሚወጣው ጡረታ ይወጣል፤ በቃኝ ብሎ የሚለቅም በቃኝ ብሎ ይለቃል።" አገሩን ለቆም የሚወጣ አለ፤ ኃብቱን በድብቅ ያሸሸ አለ ወዘተ። በልጆቹ የሚነግደው ብዙ ነው። ቁም ነገሩ፤ ስርዓቱ የፈጠረው **ድርጅታዊ ምዝበራ** ስለሆነ ስርዓቱ ካልተለወጠ ኪራይ ሰብሳቢነትና ሙስና ሊቆም አይችልም። ኃብት በቃኝ ብሎ ኪራይ መሰብሰብ ያቆመ አዲስ የስልጣን ኃብታምና የቤተሰብ አባል ፈልጌ ለማግኘት አልቻልኩም። እንዲያውም ኪራይ ሰብሳቢና ሙሰኛ ጀግና የሆነበት ኢኮኖሚ የኢትዮጲያው ነው።

ከላይ እንደቀረበው ሁሉም የፓርቲና የመንግሥት ባለሥልጣንና ተባባሪው ወፍ ዘራሽ ሃብታም በአገርና በሕዝብ ትክሻ ላይ ቁሞ ነጋዴ ከሆነ ለአገሪቱና ለድሃው ሕዝቧ ማን ሃላፊነት ይወስዳል? መንግሥትስ አለወይ የሚያስብለው ሁኔታ የትኛው ነው? ፀረ ሽብርተኛነት በተናጠል ኢትዮጵያን ታላቅ አገር ሊያደርጋት አይችልም። በማህበረሰብ ህይወት መሻሻል ስመረምረው ድርጅታዊ ምዝበራ ከሽብርተኛነት ጥቃት የተለየ አይደለም። በረሃብ መሞት የሽብርተኛነት ክስተት ነው።

ያለምንም ወንጀል ተከሶ በእስር ቤት ህይወትን ማሳለፍ የሽብርተኛነት መንጸብራቅ ነው። ኪራይ ሰብሳቢነት አድካሚ ስለሆነ በህዝቡ ላይ የሚደረግ ጥቃት ነው። ገዢው ፓርቲ ለፀረ ሽብርተኛነት ትኩረት ሰጥቶ ኢትዮጵያ እንደ ኬንያ እንዳትሆን ማድረጉ የሚመሰገን ነገር ነው። በተመሳሳይ ደረጃ በዘራፊዎች ላይ እርምጃ ለመውሰድ ለምን አይቻልም? የሚለውን ጥያቄ ሳንሠላስል መልሱ ሁሉም የበላይ ባልስልጣናት በኪራይ ሰብሳቢነትና በሙስና ስለተበከሉ ነው የሚል መልስ አቀርባለሁ።

መረጃዎች ሁሉ የሚያሳዩት አይን ያወጣ ዘረፋ ሲካሄድ መቆየቱን ነው። የስልጣን ብልግና ለአዲስ ኃብታምነት ወንፊት እንደሆነ ከላይ የተጠቀሰው ጸሃፊም በምሳሌ አቅርቦታል። “ባንድ ወቅት አንድ የገቢዎችና የጉምሩክ ከፍተኛ ባለሥልጣን ቦሌ አየር ማረፊያ ውስጥ ያለውን የጉምሩክ ቢሮ እንዲጎበኝ ማስታወሻ ይልካል።” ሚስቱ አብራው እንድትሄድ አድርጎ ሁሉንም የጉምሩክ **ኃላፊዎችና ሰራተኞች ለባለቤቱ** ያስተዋውቃል። ሴትዮዋ “የእያንዳንዱን ሰው ስም በማስታወሻ” ትይዛለች። የባለሥልጣኑ ዋና “ዓላማ” የተሰጠውን ኃላፊነት በአግባቡ ለመወጣት አልነበረም። የአየር በአየር ንግድ ዋና የሚሊየኔርነት መሰረት ስለሆነ “በሳምንቱ የባለሥልጣኑ ሚስት ዶላርዋን አጭቃ ጉዞ ወደ ዱባይ አደረገች።” በነገራችን ላይ ለአንድ ስብሰባ ዶሃና ዱባይ ከባለቤቴ ጋር ሂደን የሰማነውን አስታወሰኝ። አንድ ሱቅ ገብተን ማንነታችን እንደተናገርን፤ የሱቁ ባለቤት “ኢትዮጵያዊያን ወደዚህ ሲመጡ በአንድ ጊዜ ይዘውት የሚመጡት ዶላር ብዛት አስደንቆን ብዙዎቻችን እንደዚህ ያሉ ኃብታሞች መኖራቸው አስገረመን፤ ኢትዮጵያ ምስኪን አገር ናት ሲባል እንሰማ ነበር” ብሎ ነበር። እኛም ሁኔታውን ስለማናውቅ ይሆናል በማለት አለፍነው። ይህች የባለሥልጣን ሚስት ወደ አዲስ አበባ ስትመለስ ሁኔታውን በሚገባ ስላመቻቸችና ሰራተኞቹን ሁሉ አስቀድማ በስም ስለምታውቃቸው በመፈተሽ ፋንታ “ሻንጣዎቿን እየተሸከሙ ያለ ምንም ፍተሻና ቀረጥ ባልዋ በላከላት (የመንግሥት) ላንድሮቨር ጭነው ወደ ቤቷ ሸኟት። በዚህ መልኩ ደጋግማ የተጧጧፈ ንግድዋን በማካሄድ የናጠጠች ሃብታም ሆናለች።” የቤት መስኮት፤ በር፤ ብረታ ብረትና ሌላ ይኼን በመሰለ መንገድ ያለምንም ፍተሻና ያለ ቀረጥ ሲገባ አገሪቱ ብዙ ቢሊየን ብር ገቢ አጣች ማለት ነው። ይኼ በህብረተሰቡ ላይ ከፍተኛ ግፍና ሸክም አስከትሏል።

ከላይ የተጠቀሰችውን አይነት የባለሥልጣን ባለቤት የመሰሉ የፓርቲና የመንግሥት ባለሥልጣናት ቤተሰቦች የብዙ ሚሊየን ቪላና ሰማይ ጠቀስ ፎቆች የሚሰሩት በዚህ መልክ ነው። “ሌላው አብዛኛዎቹ የኢህአዴግና የመንግሥት (ሁለቱ ምንም ልዩነት የላቸውም) ባለሥልጣናት ሚስቶቻቸው ነጋዴዎች ናቸው።” **ድርጅታዊ ምዝበራ** በተባለው መጽሃፌ--በነጻ ስለተሰራጨ ለማንበብ ይቻላል--ያሳየሁትን ትችት በሚያንፀባርቅ ደረጃ እንዲህ ይላል። “ይህ ነገር ባጋጣሚ የሆነ ሳይሆን ሆን ተብሎ **እንደምሽግ** ለመጠቀም የታቀደ ስልት ነው። ሁሉም የሚጭበረበረው ገንዘብ የሚገባው በሚስቶቻቸው በተከፈተው ባገር ውስጥና በውጭ አካውንት ነው። የፈለገው መጠን ብር ቢገኝ ጠያቂ አይኖርም። የንግድ **ፈቃድ ደልዳላ ምሽግ** ስለሆነ፤ በውል ላጤነው በባለሥልጣናት ኃብቻ ውስጥ የእውነተኛ ፍቅር ግንኙነት ሳይሆን የመፈራረት ፍቅር ያመዘነበት ነው።” ኪራይ ሰብሳቢነትና በማጭበርበር የሚደረገው በንግድ ምሽግ ኃብት የማካበት ሂደት የስነመግባር መሻገትና ውድቀት አምጥቷል ማለቱ ነው። ከላይ ቪላዎችን ማን በደሞዙ ወይንም ጥሮ ግሮ፤ ፈጥሮ፤ አምርቶ፤ አገልግሎት ሰጥቶ ባገኘው ገቢው ለመስራት ይችላል? ብየ የጠየቅሁትን ጥያቄ ይመልሰዋል። “እየተሰሩ ያሉት የቅንጦት ቪላዎች ቢፈተሹ እውን የባለሥልጣኑ ገቢ ጋር የሚመጣጠኑ ናቸው። እያንዳንዶቹ ምንም ገቢ በሌላቸው ገና በትምህርት ላይ ያሉት የኪስ ገንዘብ ከወላጆቻቸው እጅ የሚቀበሉ **(ወጣቶች) ከ4-5** ሚሊየን ብር የሚገመት ህንጻ ባለቤት ሲሆኑ የሚያስገርም ነው።” እነዚህ ገና ስራ የሚባል ነገር ያላዩ፤ ወደፊት አገር ካልተመቻቸው የሚሰደዱ የባላሥልጣናት ልጆች የኃብት ማሸሻ ቀዳዳ ሆነዋል ማለት ነው። ይኼ ከወነጀል በላይ ወንጀል ነው።

አምባገነን ባለሥልጣናትና ቤተሰቦቻቸው ብቻቸውን ሰርቀውና የሰረቁትን ደብቀው አያውቁም። ለራሳቸው ቡድን ጥቅምና ዘላቂነት ትኩረት ስለሚሰጡ የውጭ አጋሮችና ደጋፊዎች ይፈልጋሉ፤ ለእነዚህ ያልተቆጠበ አገልግሎት ይሰጣሉ። ኢንቬስተሮች፤ የመንግሥት ያልሆኑ የውጭ ድርጅቶች፤ መንግሥታትና ልዩ ልዩ ባለሞያዎች ጥቅማቸው እስከተከበረ ድረስ አምባገነኖችንና ኪራይ ሰብሳቢዎች መደገፋቸው አይቀርም። ለእነሱ ጥሩ አገዛዝ ቢኖር ባይኖር፤ ህዝብ በረሃብ ቢሞት ባይሞት፤ ዜጎች ቢታሰሩና ቢሰደዱ ወዘተ ጥቅማቸውን አገልጋይ ቡድን እስካለ ድረስ አገዛዙን አይቃወሙም። ረሃብ አደገኛ ደረጃ ላይ ሲደርስ የምግብና ሌላ እርዳታ መስጠታቸው የሚጠበቅ ሆኗል። ቁም ነገሩ ለድሃውና ለሚራበው ህዝብ ዘላቂ መፍትሄ ለመፈለግ ፈቃደኛ አለመሆናቸው ነው። ዘላቂ መፍትሄ ለመፈለግ አገዛዙን መተቸት ይኖርባቸዋል። ለእኔ አስቸጋሪ የሆነብኝ በአንድ በኩል **ጥሩ አገዛዝ** ያስፈልጋል እያሉ በሌላ በኩል አምባገነናዊና ኪራይ ሰብሳቢ አገዛዝ ሲደግፉ መቆየታቸው ነው። ወደፊት ሊመጣ የሚችለውን መዘዝ ፍጹም ረስተውታል ማለት ነው።

በመጀመሪያ ክፍል እንዳሳየሁ፤ ጥሩ አገዛዝ የሚለው ብሂል የእድገት ጠበብቶች ሲተቹት ቆይተዋል። በዓለም ደረጃ ተቀባይነት ያለውን ትርጉም ያቀረቡት ዓለም ባንክና የተባበሩት መንግሥታት የልማት ፕሮግራም ናቸው። ከእነዚህ

በተከታታይ ተቀባይነት ያገኘውና መንግሥታት የተቀበሉት የልማት ድርጅቱን እጠቀማለሁ። ጥሩ አገዛዝ (Good Governane) ብዙ ዘርፎች አሉት፤ ከእነዚህ **"የህዝብ ተሳትፎ፤ ግልጽነትና ሃላፊነት፤ ፍትሃዊነት"** ዋናዎቹ ናቸው። እነዚህ መርሆዎች ስራ ላይ ሲውሉ "የህግ የበላይነት" ተቋማዊ ይሆናል፤ ይጠነክራል፤ ህዝብ ይቀበለዋል። በመንግሥት ላይ እምነት ይኖራል። መልካም አስተዳደር በስራ ላይ የዋለና የሚውል የጥሩ አገዛዝ ውጤት ነው። የልማት ባለሞያዎችና ተቋሞች ብዙ አመታት ወስደው ጥሩ አገዛዝ ለዘላቂና ለፍትሃዊ እድገት ወሳኝ ነው ከሚል ድምዳሜ ላይ የደረሱበት ተጻራሪው ያስከተለውን በደልና ግፍ በጥናት ስለተረዱት ነው። የፈለገው የውጭ እርዳታ እንደ ጤዝ ቢፈስ፤ ጥሩ አገዛዝና መልካም አስተዳደር ከሌሉ የእርዳታው ጉዳትና አድካሚነት ከጥቅሙ ይበልጣል። አፍሪካ ለዚህ ምሳሌ ናት። ከአፍሪካ ተዘርፎ የሚሸሸው ወደ አፍሪካ ከሚገባውና ለህዝብ ጥቅም የሚውለው ይበልጣል። ከላይ እንዳቀርብኩት፤ የኢትዮጵያ ሁኔታ ተመሳሳይ ወይንም የባሰ ነው። በአንድ በኩል ግዙፍ እርዳታ፤ በሌላ በኩል ከፍተኛ ዘረፋ እንዴት ይታረቃሉ? እድገቱ ለማነው? የሚለውን ጥያቄ በተደጋጋሚ የማነሳው የኢትዮጵያ ገዢ ፓርቲ የተባበሩት መንግሥታት የልማት ፕሮግራም ያወጣውን የጥሩ አገዛዝ መስፈርቶች ያላሟላ መሆኑን ስለተገነዘብኩ ነው።

በእኔ ግምት መልካም አስተዳደር እና ዘላቂነትና ፍትሃዊነት ያለው የእድገትና የልማት መርህ ቀጥተኛ የሆነ ግንኙነት አላቸው። አንዱ ሌላውን ያጠናክራል። መጥፎ አስተዳደር መጥፎ ውጤትን ይፈጥራል። መጥፎ አስተዳደር የአገርን ኃብትና ጥሪት ያባክናል። ለምሳሌ፤ ኪራይ ሰብሳቢነትና የአገርን አንጡራ መሬትና ሌሎችን የተፈጥሮ ጥሪቶች እንደ ተራ ነገር መነገድ የመጥፎ አስተዳደር ውጤት ነው። ህዝብን አለማሳተፍ፤ በግልጽነትና በሃላፊነት አገርን አለማስተዳደር የመጥፎ አስተዳደር ውጤት ነው። ሕዝብ ከሕዝብ ጋር ማጋጨት የመጥፎ አስተዳደር ውጤት ነው። መጥፎ አስተዳደር ለነገ የሚል እሴትን አያጠናክርም፤ "እኔ ከሞትኩ ሰርዶ አይብቀል" የሚለውን አመለካከት ያጠናክራል። መጥፎ አስተዳደር ዜጎች የተፈጥሮ አደጋ ሲደርስባቸው በፍጥነት አይደርስላቸውም። የህግ የበላይነት ስለሌለ የተጎዱ ዜጎች አቤቱታ ለማቅረብ የሚችሉበት ታማኝ ተቋም የለም። ሌላው ቀርቶ ሰላማዊ ሰልፍ ለማድረግ አይችሉም። ራሱን ብቻ አውራና ኃብታም ያደረገ ቡድን የሚጠቅመው ራሱንና ደጋፊዎቹን ነው። የድርቅ ረሃብ ሲከሰት የችግሩን ከባድነትና አስከፊነት አይቀበልም። ይባስ ብሎ ችግሩን ለመደበቅ ይሞክራል። ከፓርቲው ቁጥጥር ነጻ የሆኑ ድርጅቶች ስለማይፈቀዱ ህዝቡ እውነተኛ ዜና አያገኝም።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ከድርቅ የሚከሰት ተከታታይና ተደጋጋሚ ችግርና የድብብቆሽ ጨዋታ ለምዶታል። የድርቅ ረሃብ እያለ የለም ማለት፤ ኢትዮጵያዊያን እየሞቱ  የሚሞተው "ከብት፤ ግመል፤ አህያ ወዘተ" ነው፤ ሰው አይሞትም ማለት ተቀባይነት የሌለው መልእክት በአፄ ኃይለ ሥላሴ፤ በደርግና በአሁኑ ገዢ ፓርቲ ተነግሯል። እነዚህ ሶስት አምባገነን መንግሥታት የተጎዱ ህጻናትን፤ እናቶችን፤ አባቶችን ከማዳን ይልቅ ትኩረት የሰጡት ለራሳቸው ዝና ነው። ለህሊና የሚቀፈው ሶስቱም አገሪቱ የማትችለውን የባጀት ወጭ ለግልና ለቡድን ዝና ፈሰስ አድርገዋል። የአሁኑን የድርቅ ረሃብ ከበፊተኞቹ ለየት የሚያደርገው ገዢው ፓርቲና እንደ ዓለም ባንክ ያሉ አበዳሪና ለጋስ ድርጅቶች የሚያደንቁትን፤ ኢትዮጵያ ባለፉት አስር ዓመታት፤ በተለይ ከምርጫ ዘጠና ሰባት በኋላ፤ "አስደናቂ እድገት አሳይታለች" የሚለውን ፖሮፓጋንዳ ነው። ገዢው ፓርቲ ባለፉት ሃያ አራት አመታት <u>**ለልማት ድጎማ ብቻ $40 ቢሊየን እርዳታ**</u> አግኝቷል። ያለፉት ሁለት መንግሥታት ያገኙት እርዳታ ተደማምሮ የአሁኑ ገዢ ቡድን በሁለት ዓመታት ካገኘው አይደርስም። ይህ ግዙፍ እርዳታ የተለገሰው ለኢትዮጵያ ድሃ ህዝብ ነው። ሆኖም፤ ዋናው ተጠቃሚ ግን ህዝቡ ነው ለማለት የሚያስደፍር፤ በመሬት የሚታይ ሁኔታ የለም። ዓለም ባንክ ያወጣው <u>**የቅርብ ዘገባ 37**</u> ሚሊየን ህዝብ ድሃ እንደሆነ ያሳያል። ወጣት ትውልድ በገፍ ከሚሰደድባቸው አገሮች መካከል ኢትዮጵያ ከፍተኛውን ደረጃ ይዛለች። የተባበሩት መንግሥታት፤ ቢቢሲና ሌሎች የውጭ ተቋሞች በተደጋጋሚ እንዳሳሰቡት <u>**በቅርቡ 8.2 ሚሊየን ህዝብ**</u> በረሃብ ላይ ይገኛል፤ እርዳታ በፍጥነት ካልደረሰለት የሚራበው ህዝብ <u>**ብዛት 15 ሚሊየን ይደርሳል።**</u> ብዙ ረሃብተኞች ቀያቸውን እየለቀቁ ወደ ከተሞች በመሰደድ ላይ ይገኛሉ፤ በመርካቶ አካባቢ የሰፈሩትን ረሃብተኞች ትክክለኛ ቁጥር ለማወቅ ባይቻልም፤ ብዙ እንደሆኑ ለመገመት አያስቸግርም።

ይኼን ከድርቅ የተከሰተ ረሃብ ለመደበቅ አይቻልም። አንደኛ ረሃብ መኖሩ ይፋ ሆኗል፤ ሊሸሸግ አይችልም። ሁለተኛ በአፄ ኃይለ ሥላሴ መንግሥትና በደርግ ዘመኖች የነበረው <u>**የመገናኛ ሁኔታ**</u> በጣም ተቀይሯል። ኢትዮጵያ እንደ ኬንያና ሶማሊያ ዘመናዊ መገናኛ ተስፋፍቶባታል ለማለት ባይቻልም፤ ኢንተርኔት፤ ዘመናዊ የማህበረሰብ መገናኛ፤ ለምሳሌ ሞባይል በገጠር ተሰራጭቷል። ሶስተኛ፤ የተባበሩት መንግሥታት የምግብ ድርጅት ረሃቡን ለመወጣት አስቸኳይ የምግብ ድጋፍ እንደሚያስፈልግ በተደጋጋሚ ተናግሯል። አራተኛ፤ የመንግሥት ያልሆኑ የውጭ አገሮች የሰብአዊ አገልግሎት ድርጅቶች አገሪቱን ልክ እንደ ወረርሽኝ አጥለቅልቀዋታል;፡ በኢትዮጵያ ያለውን ሁኔታ ያውቁታል። እነዚህ ተቋሞች የተራቡ ኅጻናትን እየመገቡ ነው። ጥቂቶቹን በስልክ ሳነጋግር የድርቁ ረሃብ አሳሳቢ መሆኑን ተናግረዋል። ረሃቡን ምክንያት አድርገው ገንዘብ የሚሰበስቡም አሉ። በመጨረሻ ሩህሩሁ የኢትዮጵያ ህዝብ በየቤቱ፤ በየቤተክርስቲያኑና በየመስጊዱ እርዳታ እንስጥ የሚል ድምፅ ያሰማል። ስለሆነም፤ ገዢው ፓርቲ የመገናኛ ብዙሃን እገባ ቢያደርግም ረሃቡን ለመደበቅ አይቻልም። የሚሻለው

የችግሩን ግዙፍነት ተቀብሎ ለተራቡት በአስቸኳይ መድረስና ለወደፊቱ የድርቅ ረሃብ **<u>እንዳይከሰት የፖሊሲና የመዋቅር</u>** ተግዳሮቶችን መወጣት ነው። ዘላቂው መፍትሄ ጥሩ አገዛዝ ለመመስረት ደፍሮ መነሳትን ይጠይቃል። አንዱ በግልፅ የሚታይ ችግር በድሃው ህዝብ ስም የሚነግዱና ኪራይ ሰብሳቢዎች ዲሞክራሳዊ አገዛዝ እንዳይመሰረት ማነቆ መሆናቸው ነው። እነሱ በድሎት እስከኖሩ ድረስ ደንታ ያላቸው አይመስሉም።

በአጠቃላይ ሲታይ ለገዢው ፓርቲ አይዋጥለት ያለ አስኳል ጉዳይ አለ። በዓለም ደረጃ አስደናቂ እድገት አለ ብሎ በተከታታይ ስለተናገረ ረሃብተኛውን ለመመገብ አቅም አለኝ ብሎ ማስተጋባት አስፈላጊ ሆኗል። እርግጥ ነው አንድ ሰሞን ገዢው ፓርቲ የኢትዮጵያ የእርሻ ምርት እድገት **<u>በአመት "14 በመቶ ደርሷል"</u>** ማለቱ ትዝ ይለኛል። እንደዚህ ያለ የእድገት ተመን ስኬታማ ለማድረግ የአምራቹ ህዝብ አቅም ከፍተኛ ደረጃ ላይ መድረስ አለበት። በየአካባቢው ጎተራዎች መሙላት ነበረባቸው። ጎተራዎች ከሞሉ ለክፉ ቀን የሚሆን በቂ ምግብ አለ ማለት ነው። ካለ ከውጭ ስንዴና ሌላ መሸመት አስፈላጊ አይሆንም ማለት ነው። ልመና አያስፈልግም ማለት ነው። ይኼ ከሆነ ገዢው ፓርት ለምን የአገር ውስጥና የውጭ እርዳታ ይጠይቃል? የሚለምነውን ለምን ይደብቃል? አገሪቱ ከማትችልበት ደረጃ ላይ ከደረሰች ለምን ግልፅነት አይኖርም? ለምን ለህዝብ ሃላፊነት አይኖርም? ለምን ችግሩን መደበቅ አስፈለገ?

ይህን ክፍል ለመደምደም፤ ኪራይ ሰብሳቢዎች ስርዓቱን ለራሳቸው የድሎትና የቅንጦት ኑሮ ለመጠቀም እስከቻሉ ድረስ ከድርቅም ሆነ ከሌላ የሚከሰትን ረሃብ ለመቅረፍ አይቻልም።

ይቀጥላል